## በቁኒስ ይነዳል፣
## አዲስ ላይ ይጨሳል!

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

**ለነሱ፣ ለዘመነኞቹ!**

« እዚያ ማዶ ጭስ ይጨሳል፣
አጋፋሪ ይደግሳል፣
ያንን ድግስ ውጬ ውጬ፣
በድንክ አልጋ ተገልብጬ፣ »
ቁንጣን ይዞኝ ታምሜያለሁ፣
አትቀስቅሱኝ ተኝቻለሁ::

**ለ'ኛ፣ ለኢትዮጵያ ልጆች!**

«እዚያ ማዶ ጭስ ይጨሳል፣
አጋፋሪ ይደግሳል፣
ያንን ድግስ ሳሽት ውዬ፣
ጠሜን አደርኩ ተጠቅልዬ፣
ሆያ ሆዬ ጉዴ !
ነፃነቴን ይላል ሆዴ !
ኧረ ቢቃ ! ቢቃ !
ከድብርትህ ንቃ !
ሊፀምሮህን እንቃ ! »
……በጎደለ እናንተ ሙሉበት፣

በጎረቤት ይነዳል፣
በኛ ቤት ይጨሳል! ፣
በደሉ ገንፍሏል፣
ዘረኝነት ነግሷል፣
ኑሮ ያጠዘናል፣
አገር ተሸጦ ሕዝብ ያለቅሳል፣
ጀግና ጠፍቶ አገር ሞቷል፣
ነፃነት ተቀብሯል::

«እባብ ለባብ፣
ካብ ለካብ» ይተያያል፣
በዳይና ተበዳይ ይገለማመጣል፣
አንዱ ሌላውን ያጠምዳል፣
በዳይ ለተበዳይ ልፋጭ ቢጤ ይጥላል፣
ተበዳይ በልፋጭ ሲጣላ በዳይ እንደገና ይገላል::

*እዚያ ማዶ !*

*ተቃዋሚው ላይስማማ ተስማምቷል፣*
*በየወንዙ ይማማላል፣*
*ሟች ሟች ምሎ: ማታ ማታ ይከዳዳል፣*
*ተማሪው ተኝቷል፣*
*ያንቀላፋል፣*
*ተጋድሞ ያንኮራፋል::*
*ምሁር ነኝ ባይ አድፍጧል፣*
*ወይ በሆዱ ተደልሏል፣*
*ዲያስፖራው ይቆዝማል፣*
*ውስኪ ቢራ ይጨልጣል፣*
*ከረምቡላ ያቃጭላል፣*
*ያገር ጉዳይ ችላ ብሏል፣*
*ግን ሕዝቡ ይጮሃል፣*
*የወገን ያለህ ይላል፣*
*የሚሰማው አቶ ይባጃል ይባዝናል::*

*ቡዳዎች ያሾፋሉ፣*
*በዘር ከፋፍለው ይገዛሉ፣*
*ያስራሉ ይገርፋሉ፣*
*ያሻቸውን ይገላሉ፣*
*ሕፃናትን ይሸጣሉ፣*
*ያገር ንብረት ይዘርፋሉ፣*
*ካገራችን ያሸሻሉ፣*
*በውጭ ባንክ ያጉራሉ ያጉራሉ::*

*ጨለማው በንጋት ሊቀየር፣*
*የጨሰው መንደዱ ላይቀር፣*
*አናዳጅና ተናዳጅ ሊናደድ፣*
*አንዱ እሳት ሆኖ ሌላው አመድ፣*
*ይተያያሉ ክብሪት ይዘው ፣*
*አንዱ ሌላውን ሊያነደው፣*
*ጨለማው ተቀዶ ጎህ እንዲቀድ፣*
*ክብሪቱን ጫረው የጨሰው ይንደድ::*

*ተበዳይ ድፈር ተደፋፈር፣*
*እርስ በርስ ተማመን ተፋቀር፣*
*ቢነድ እሳቱ ቢጫር፣*
*ከበደል ሌላ ምን ሊቀር?!*
*የጨሰው ይንደድ፣*
*በደልና ግፍ ይወገድ፣*
*የዘር ግንብ ይፍረስ፣*
*አምባ ገነን ይገርሰስ፣*
*ነፃነት ተመልሶ ይንገስ፣*
*ዕድገት ዝራ ተስፋን ጫር፣*
*አብቅል የነፃነት የኩልነት የወንድማማችነት አገር::*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!*
*እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ!*

*ጥር 6 2003 ዓ.ም. January 14/2011*